ሁለት ሙስሊሞች ተገናኝተው በእጅ በመጨባበጥ ሰላምታ ከተለዋወጡ ከመለያየታቸው በፊት ለነርሱ ወንጀላቸው ይማራል።

ከበራእ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል: "ሁለት ሙስሊሞች ተገናኝተው በእጅ በመጨባበጥ ሰላምታ ከተለዋወጡ ከመለያየታቸው በፊት ለነርሱ ወንጀላቸው ይማራል።"»
[ከሁሉም ሰነዶቹ አንፃር ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ሁለት ሙስሊሞች በመንገድና መሰል ቦታ ተገናኝተው አንዱ ሌላኛውን በእጅ በመጨባበጥ ሰላምታ ከተሰጣጡ ለነርሱ (ከቦታው) በአካል ወይም ከመጨባበጡ እጃቸውን ከማለያየታቸው በፊት ወንጀላቸው ይማራል ብለው ተናገሩ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/6257